Prime Minister's Office

משרד ראש הממשלה
የጠቅላይ ሚኒስቴር ቢሮ

ከጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የወጣ የጥሪ መግለጫ

የኢትዮጵያ ይሁዳውያን ከኢትዮጵያ ተነስተዉ በሱዳን በኩል ወደ እሥራኤል ሲሻገሩ በሞት የተለዩትን ለማስታወስ የተነደፈ ፕሮጀክት

ሀ . የእሥራኤል መንግሥት የኢትዮጵያ ይሁዲዎች ከኢትዮጵያ ተነስተዉ በሱዳን በኩል ወደ እስራኤል ጉዞ ላይ እንዳሉ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩትን ቤተዘመዶቻቸውን ሥም ለማስታወስ በሃር ሄርጹል በሚቋቋመዉ የሙታን መታሰቢያ ሀዉልተ ድንጋይ ላይ እንዲጻፍ ህዳር 27 ቀን 2011 ዓ.ም ባጸደቀዉ ዉሳኔ ቁጥር 3885 መሠረት ይጻፋል።
የሙታን መተሰቢያ ፕሮጀኬት ስራዎች የሚፈጽመዉ የሂስታድሩት ሃጲዮኒት ድርጅት ሲሆን የገንዘብ እርዳታ የለገሱት የእሥራኤል መንግሥትና የሶሁኑት ሃይሁዲት መ/ቤት ናቸዉ።

ለ. የእሥራኤል መንግሥት ያስተላለፈዉን ዉሰኔ ተግባር ላይ ማዋል ይቻል ዘንድ የምክር አገልግሎት የሚሰጥ ልዩ ኮሚቴ ተቋቁሞ የሚቾችን ስም ለማሰብ (ክራይቴሪያ) መሰፈረቶችን ነድፏል። የኮሚቴዉ መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸዉ፡-

1. ከጥር ነ ቀን 1979 ዓ.ም እስከ ታህሳስ 31 ቀን 1990 ዓ.ም በሱዳን በኩል ወደ እስራኤል ለመምጣት ጉዞ ላይ እንዳለ የሞተ ωψμ በሱዳን በርሃ ጉዞ ላይ እንዳለ በሞት የተለየ።

2. ሚቹ በሞት የተለየዉ ወደ እስራኤል ለመሻገር ወደ ሱዳን ጉዞ ላይ እንዳለ ኢትዮጵያ ዉስጥ ወይም ሱዳን ዉስጥ በሰዉ እጅ ተገድሎ ከሆነ።

3. በሞት የተለየዉ ከማይታወቅ ቦታ ተቀብሮ ከሆነ ወይም ከይሁዳዉያን መካነ መቃብር ዉጭ ተቀብሮ ከሆነ።

ሐ. ከዚህ በላይ በተጠቀሱት መመሪያ መስፈረቶች መሰረት ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ይሁዳዉያን በሱዳን በኩል ወደ እሥራኤል ለመምጣት ሲሉ በጉዞ ላይ እንዳሉ ሙተዉ የቀሩ ዉድ የቤተሰብ አባላት ሥም ዝርዝር ለሚመለከታቸዉ ሰብሳቢዎች እንድታስተላልፉ በትህትና ትጠየቃላችሁ።
በህወት ያሉ የሚች ቤተሰቦች ወይም ዘመዶቹ ባይሆኑም ሲሞት አብረዉት የነበሩ ሰዎች የሚያስተላልፉት የምስክርነት ቃል በምስክቶች ቃል መቀበያ ቅጽ/ቶፌስ ላይ ይመዘገባል። ቅጹን ወይም ቶፌሱን የሚሞሉት ሰብሳቢዎች ሲሆኑ በርካታ የኢትዮጵያ ይሁዳዉያን በሚኖሩባቸዉ ከተማዎች እየሄዱ ወደ የቤተሰብ አባል በሞት የተለያቸዉ ቤተሰቦች የምስክርነት ቃል ይቀበላሉ። ሰብሳቢዎች የምስክርነት ቃል ለመቀበል ወደ ተለያዩ ከተማዎች ከመሄዳቸዉ በፊት አስቀድመዉ የሚመጡበትን ቀንና ስዓት ያስታዉቃሉ።

መ. ስለሞቱት ሰዎች የምስክሮች ቃል የመቀበል ሂደት ሲፈጸም መረጀዎች ለአጣሪ ኮሚቴ ይተላለፉና በሙታን መታሰቢያ ሀዉልት ድንጋይ የሚጻፉትን ሚቾዎች ስም ዝርዝር ያጸደቃል። ኮሚቴዉ ዉሳኔዉን በይፋ ካስታወቀበት ቀን አንስቶ በ21 ቀናት ዉስጥ የሚች ቤተሰቦች አቤቱታ ማቀረብ ይችላሉ።

ሰ. አጣሪዉ ኮሚቴ የተዋቀረዉ በአምስት አባላት ሲሆን የኮሞቴዉ ሊቀ መንበር ፕሮፌሰር ሚካኤል ኮሪናልዲ ናቸዉ። ሌሎች የኮሚቴዉ አባላት በሱዳን በኩል ወደ እስራኤል የመጡ ከኢትዮጵያ ይሁዳዉያን ቤተሰብ የተወለደ ወይም የተወለደች የህግ ጠበቃ ባለ ሙያ ፤ በኢትዮጵያ ጎንደርና ትግራይ ከፍላተ ሃገራት ፤ በወልቃይትና ጀሯ የመጡ ሶስት የህዝብ ተወካዩች ፤ በአማርኛ፤ ትግርኛና እብራይስጥ ቋንቋዎች የመጻፍና የመናገር ችሎታ ያላቸዉ ናቸዉ።

ረ. የሙታን መታሰቢያ ፕሮጀክት በተበለከተ ጥያቄ ካላችሁ ወይም ተጨማሪ ማብራሪያ ለመቀበል የኢትዮጵያ ይሁዳዉያን መታሰቢያ ፕሮጀክት ሥራ አስካሃጅ ለአቶ ጻሂ ይስማኒ በለጠ በስልክ ቁጥር **02-6202536/7** ደዉሉ።
ወይም በኢሜል TzionaM@wzo.org.il መልእክት ማስተላለፍ ትችላላችሁ። ኢንተርኔት ድረ ገጽ- www.wzo.org.il.